## 1. ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ምን ማለት ነው?

***ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም*** ማለት በአለም አቀፍ ገበያ የአቅርቦት ሠንሰለት ላይ ተሳትፎ ያላቸው፤ ለጉምሩክና ታክስ እንዲሁም ለሀገሪቱ ህጎች ታማኝ የሆኑ እና በዓለም ጉምሩክ ድርጅት የተቀመጡ የደህንነትና የህግ ተገዥነት መስፈርቶችን የሚያሟሉ እንዲሁም በአሰራርና ሲስተም ኦዲት አልፈው ኃላፊነት የሚወስዱ መሆናቸው በጉምሩክ ሲረጋገጥ በሚሰጣቸው የእውቅና ሰርተፍኬት መሰረት በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ እንዲስተናገዱ የሚመረጡ ድርጅቶች የሚታቀፉበት የአሰራር ስርዓት ነው፡፡

***በዚህም መሰረት በዚህ ፕሮግራም የሚታቀፉ ድርጅቶች:***

- በአለም አቀፍ ገበያ የአቅርቦት ሠንሰለት ላይ ተሳትፎ ያላቸው፣
- ለጉምሩክና ታክስ እንዲሁም ለሀገሪቱ ህጎች ታማኝ የሆኑ እና
- በአሰራርና ህግ ተገዥነት ኦዲት አልፈው ኃላፊነት የሚወስዱ መሆናቸው ሲረጋገጥ ቀልጣፋና ፈጣን የጉምሩክ አገልግሎት እንዲሰጣቸው በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ እንዲስተናገዱ የሚመረጡ ድርጅቶች ናቸው፡፡

## 2. የፕሮግራሙ ዓላማ

ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ዋና ዓላማ ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸው ድርጅቶች በገቢና ወጪ እቃዎች ላይ በሚደረግ ቁጥጥር መጉላላትን በመቀነስ የንግድ ደህንነትን አስተማማኝ በማድረግ ንግድን ማሳለጥ ነው፡፡

**የፕሮግራሙ ዝርዝር ዓላማዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡**

- ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ያላቸውን ድርጅቶች ፈጣን አገልግሎት በመስጠት ንግዱን ለማሳለጥ፣
- ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው ላይ ትኩረት በማድረግ ሊፈጠሩ የሚችሉ የደህንነት ስጋቶችን ለመቀነስ፣
- ቀረጥና ታክስን በፈቃደኝነትና በራስ ተነሳሽነት የመክፈል ባህልን ለማዳበር፣
- የአምራች ኢንዱስትሪና ላኪዎችን በማበረታታት ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለመደገፍ፣
- ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር አጋርነትን በማሳደግ ተገማችና ቀልጣፋ የጉምሩክ አገልግሎት ለመስጠት፣


*By Talema Ayele, Email address iffso143@gmail.com, Mob. Number 09-12-75-96-55, AEO principal officer*

## 3. <u>የፕሮግራሙ መነሻ</u>

ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም መነሻ እ.ኤ.አ መስከረም 11/2001 በአሜሪካ የተፈፀመውን የሽብር ጥቃት ተከትሎ የአሜሪካ መንግስት ከሽብር ጥቃቱ በኂላ የሚፈጠሩ የደህንነት ስጋቶችን ለመቀነስ የጉምሩክ አስተዳደር ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር ተቀራርቦ በመስራት የሚፈጠሩ የደህንነት ስጋቶችን ለመቀነስ የበኩሉን ሚና ለመወጣት እንዲችል **"የጉምሩክና የንግዱ ማህበረሰብ አጋነት ሽብርተኝነትን ለመከላከል/Customs Trade Partnership against Terrorism (C-TPAT)"** በሚል ፕሮግራም የተጀመረ ነው፡፡ የዚህ ፕሮግራም ዋና ዓላማም ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር ተቀራርቦ በመስራት ህጋዊ ንግድን ማሳለጥ እና የሚፈጠሩ የደህንነት ስጋቶችን መቀነስ ነው፡፡

በመቀጠልም የአለም ጉምሩኮች ድርጅት (WCO) እ.ኤ.አ በ2005 በዓለም አቀፍ ንግድ የእቃዎች ዝውውር ሂደት የገቢና ወጪ እቃዎች በጠረፍ አካባቢ በሚደረግ ፍተሻ ሳይስተጓጎሉ አስተማማኝ ፈጣን አገልግሎት እንዲሰጣቸው እና ደህንነትን ለማረጋገጥ እንዲቻል Safe Framework of Standards የሚል አሰራር ዘርግቷል፡፡ የዚህ ስታንዳርድ ዋና ዓላማም  ንግድን ማሳለጥ እና የንግድ አካባቢውን ደህንነት አስተማማኝ ለማድረግ ሲሆን ሃያ ዘጠኝ (29) ስታንዳርዶችን በሶስት ዋና ዋና የትብብር ምሰሶዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሲሆን ሶስቱ ዋና ዋና የትብብር ምሰሶዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በጉምሩክ አስተዳደሮች መካከል የሚደረግ ትብብር፣
- በጉምሩክ አስተዳደርና  በንግዱ ማህበረሰብ የሚደረግ ትብብር፣
- በጉምሩክና በሌሎች የመንግስት አስፈፃሚ መ/ቤቶች መካከል የሚደረግ ትብብር ናቸው፡፡

በዚህም መሰረት ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም የዓለም ጉምሩክ ድርጅት ካስቀመጣቸው የትብብር ምሰሶዎች የሁለተኛው የትብብር ምሰሶ (በጉምሩክና በንግዱ ማህበረሰብ የሚደረግ ትብብር) ማስፈፀሚያ ዋና መሳሪያ ነው፡፡

## 4. <u>ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም በኢትዮጵያ</u>

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ከትኩረት መስኮች አንዱ የንግድ ማህበረሰቡ ለህግ ተገዥ እንዲሆን በማድረግ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ ማድረግ ነው፡፡ ለዚህም


*By Talema Ayele, Email address iffso143@gmail.com, Mob. Number 09-12-75-96-55, AEO principal officer*

የትኩረት መስክ ማስፈፀሚያ ከተዘረጉት የጉምሩክ አሰራሮች ውስጥ ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም አንዱ ነው፡፡

ፕሮግራሙ በሙከራ ደረጃ በ2001 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ጥያቄ ለሚያቀርቡ ድርጅቶች የመምረጫ መስፈርቱ ለላኪዎች እና ኢንዱስትሪ አምራቾች ልዩ ትኩረት የሚሰጥ መሆን እንዳለበት የጉምሩክ አዋጅ 859/2006 (እንደተሻሻለ) ይደነግጋል፡፡

## 5. <u>በፕሮግራሙ የሚታቀፉ ድርጅቶች</u>

የዚህ ፕሮግራም ተጠቃሚ ለመሆን ጥያቄ ማቅረብ የሚችሉት በዓለም አቀፍ ንግድ የአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ በቀጥታ ተሳትፎ ያላቸው በማንኛውም የንግድ ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ናቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ፡-

- አስመጪዎች፣
- ላኪዎች፣
- አምራቾች፣
- ትራንዚተሮች፣
- አጓጓዦች፣
- የመጋዘን ኦፕሬተሮች፣
- ደረቅ ወደቦችና
- ሌሎችም በሎጀስቲክስ ዘርፍ ላይ ዓለም አቀፍ ሚና ያላቸው ድርጅቶች በዚህ ፕሮግራም ለመታቀፍ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

## 6. <u>በፕሮግራሙ ለመታቀፍ የመመዘኛ መስፈርቶች</u>

በመሆኑም ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች ፕሮግራም ለመታቀፍ የሚያመለክቱ ድርጅቶች ከአቅርቦት የንግድ ሰንሰለታቸውና ከሚከተለሉት የንግድ ስራ እንቅስቃሴ አንፃር ኮሚሽኑ በሚያዘጋጀው አለም አቀፍ ደረጃው በጠበቀ መስፈርት መሰረት የቅድመ ኦዲት መስፈርቶችን እና የመመዘኛ መስፈርቶችን ማለፍ/ማሟላት አለባቸው፡፡

6.1. **<u>የቅድመ ኦዲት መስፈርቶች</u>**፡- የቅድመ ኦዲት መስፈርት ማለት አመልካች ድርጅቶች በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ጥያቄያቸውን እንዳቀረቡ የውስጥ አሰራርና ህግ ተገዥነት ኦዲት


By Talema Ayele, Email address iffso143@gmail.com, Mob. Number 09-12-75-96-55, AEO principal officer

ሂደት ከመጀመሩ በፊት የሚከተሉት የቅድመ ኦዲት መስፈርቶች በሙሉ/ሁሉም መሟላት አለባቸው፡፡

- የስጋት ደረጃው ቢያንስ መካከለኛ (Yellow) መሆን አለበት፤
- ባለፉት ሁለት ዓመታት በጉምሩክ እና በሀገር ውስጥ ገቢ የተገኘበት የኦዲት ግኝት መጠን አጠቃላይ ከከፈለው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ከ5% ያልበለጠ መሆን አለበት፤
- ቢያንስ ቢያንስ የድርጅቱ የፋይናንስ እና የመጋዘን አስተዳደር የስራ ክፍሎች በመረጃ ቴክኖሎጂ የተሳሰሩ መሆን አለባቸው፤
- የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ላይ ካልሆነ በስተቀር ያለፈው አንድ አመት ኪሳራ ላይ መሆን የለበትም፤

እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟሉ ድርጅቶች በአሰራርና ህግ ተገዥነት ኦዲት ከታች ባሉት የመመዘኛ መስፈርቶች ተመዝነው ማለፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡

6.2. <u>በአሰራርና ህግ ተገዥነት ኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች</u>፡- የአሰራርና ህግ ተገዥነት ኦዲት ማለት በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ጥያቄ የሚያቀርቡ ድርጅቶች የቅድመ ኦዲት መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ በፕሮግራሙ ለመታቀፍ የተቀመጡ ዝርዝር የመመዘኛ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በሚሰበሰቡ መረጃዎች መሰረት እና በድርጅቱ የስራ ቦታ በአካል በመገኘት የድርጅቱ የውስጥ አሰራር በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ብቁ መሆኑን የማረጋገጥ ሂደት ነው፡፡

በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ማመልከቻ ያቀረበ ድርጅት ሁሉንም የቅድመ ኦዲት መስፈርት የሚያሟላ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ በቀጣይ በአሰራርና ህግ ተገዥነት ኦዲት የሚመዘንባቸው ጥቅል መስፈርቶች ስድስት ሲሆኑ በእያንዳንዱ ጥቅል መስፈርት ውስጥ ብዙ ዝርዝር መስፈርቶችን የሚያጠቃልል ነው፡፡

*ሀ/ **የድርጅቱ የህግ ተገዥነት ታሪክ** (35%)*፡- ድርጅቱ በጉምሩክና ሃገር ውስጥ ታክስ ያለው የህግ ተገዥነት ታሪክ መረጃ መሰረት ተገቢውን የጉምሩክና ታክስ ክፍያ በፈቃደኝነት የሚከፍልና በኦዲት ከፍተኛ ግኝት የሌለበት መሆን ይኖርበታል፡፡

*ለ/ **የድርጅቱ የሎጂስቲክስና ሀብት አመራር ስርዓት** (15%)*፡- ድርጅቱ ስታንዳርዱን የጠበቀ የገቢና ወጪ እቃዎች የሎጂስቲክስ ስርዓት ያለው እና ለሁሉም የስራ ክፍሎች ስታንዳርዱን የጠበቀ የውስጥ የአሰራር ስርዓት ያለውና የገቢና ወጪ እቃዎች ላይ ተገቢውን ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ያለው መሆን አለበት፡፡


*By Talema Ayele, Email address iffso143@gmail.com, Mob. Number 09-12-75-96-55, AEO principal officer*

***ሐ/ ድርጅቱ ለአገር ኢኮኖሚ የሚያደርገው አስተዋፅኦ (15%)፡-*** በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ጥያቄ የሚያቀርብ ድርጅት ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት ለመንግስት የከፈለው አማካኝ የግብር መጠን፣ አማካኝ ሽያጭ፣ አማካይ ትርፍ፣ የፈጠረው የስራ እድል መጠን እና ሌሎች ማህበራዊ አስተዋፅኦዎች ከፍተኛ ሚና ያለው መሆን ይጠበቅበታል፡፡

***መ/ የድርጅቱ የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት (15%)፡-*** ድርጅቱ የውስጥ አሰራሩን በመረጃ ቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ የመጋዘን፣ የፋይናንስ እና ሽያጭ የስራ ክፍሎች ወቅታዊ በሆነና በተሻሻለ የመረጃ ቴክኖሎጂ የተሳሰሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ መረጃዎች ዘላቂና አስተማማኝ በሆነ የመረጃ አያያዝ ስርዓት መያዝ ያለባቸው ሲሆን ጉምሩክ ኦዲት ማድረግ በፈለገ ጊዜ ሊደረስባቸው የሚችልና ግልፅ የሆነ የመረጃ አስተዳደር ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡

***ሠ/ የድርጅቱ የፋይናንስ አቅም (10%)፡-*** በዚህ ጥቅል መስፈርት ውስጥ ድርጅቱ የአጭር ጊዜ እዳውን ለመክፈል ያለው አቅም፣ የኢቨስትመንት አዋጭነት ትንታኔ እና ኢንቨስትመንቱን ለመመለስ የሚፈጀውን የጊዜ ትንታኔ በመስራት የድርጅቱ የፋይናንስ አቅም ውጤት ድርጅቱ ኪሳራ ሳያጋጥመው ቀጣይነት ያለው መሆኑን የሚያመላክት መሆን ይጠበቅበታል፡፡

***ረ/ የድርጅቱ የደህንነት መስፈርቶች (10%)፡-*** የድርጅቱ የመረጃ አያያዝ ደህንነት፣ የሰራተኞች ደህንነነት፣ የኮምፒውተርና መረጃ አያያዝ ደህንነት አስተማማኝ መሆን አለበት፡፡ በዋና ዋና የስራ ክፍሎችና በድርጅቱ የመግቢያና መውጫ በሮች ላይ የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች ያሉት እና በመግቢያና መውጫ በሮች ጥብቅ ቁጥጥር የሚያደርግ መሆን ይጠበቅበታል፡፡

## 7. <u>በፕሮግራሙ ለመታቀፍ ብቁ የሚያደርግ ውጤት</u>

የቅድመ ኦዲት መስፈርቶችን በማሟላት በዝርዝር የመመዘኛ መስፈርቶች መሰረት የአሰራርና ህግ ተገዥነት ኦዲት ሂደት በማለፍ በኦዲት ውጤት መሰረት 75 እና ከዚያ በላይ ያስመዘገበ ድርጅት በፕሮግራሙ እንዲታቀፍ በሚቀርብ የውሳኔ ሃሳብ መሰረት በኮሚሽኑ ከፍተኛ አመራር የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡


*By Talema Ayele, Email address iffso143@gmail.com, Mob. Number 09-12-75-96-55, AEO principal officer*